# የኢንፍሉዌንዛ ክትባት ለነፍሰ ጡር ሴቶች

*የኢንፍሉዌንዛ በሽታ በነፍሰ ጡር ሴቶች ላይ እንደሌሎች ሴቶች የተለመደ ነው ሆኖም ግን እርጉዝ ሴቶች ለከባድ በሽታ የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው። የእርግዝናው ጊዜ በጨመረ ቁጥር አደጋው ይጨምራል። እናት በጠና ከታመመች ይህ ለፅንሱም አደገኛ ነው። ለነፍሰ ጡር ሴቶች የሚሰጠው ክትባት እናትና ልጅን ይጠብቃል።*

**ምክር ለነፍሰ ጡር ሴቶች**
በ 2 ኛ እና በ 3 ኛ የእርግዝና ደረጃ ውስጥ ያሉ ነፍሰ ጡር ሴቶች ከኢንፍሉዌንዛ ወቅት በፊት እንዲከተቡ ይመከራል። በአንደኛ የእርግዝና ደረጃ ውስጥ ያሉ ነፍሰ ጡር ሴቶች ሌላ ተጋላጭ ቡድን ውስጥ የሚመደቡ ከሆነ ክትባት እንዲወስዱ ይመከራል።

ይህ ምክር ለኢንፍሉዌዛ ወቅት ነው (መኸር እና ክረምት)

**እናትን ይጠብቃል**
ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የኢንፍሉዌንዛ ክትባት እንደሌሎች ጤናማ ጎልማሶች ሁሉ ለነፍሰ ጡር ሴቶች ጥሩ መከላከያን ይሰጣል።

**ልጁን ይጠብቃል**
ጨቅላ ሕፃናት ከትላልቅ ልጆች እና አዋቂዎች በበለጠ ለከባድ የኢንፍሉዌንዛ ህመም የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በእርግዝና ወቅት እናት ክትባት ከወሰደች ልጁ ከተወለደ በኋላ ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራቶች ከቫይረሱ ጥበቃ ያገኛል። በእርግዝና ወቅት የኢንፍሉዌንዛ ክትባትን መውሰድ የፅንስ መጨንገፍ ፣ ያለጊዜው መወለድ ወይም በፅንሱ ላይ የሚደርስን ጉዳት አይጨምርም።

**ስለ ኢንፍሉዌንዛ ክትባት**
ለነፍሰ ጡር ሴቶች የሚመከረው የኢንፍሉዌንዛ ክትባት በአንድ መጠን የሚሰጥ ሲሆን ክትባቱም ትንሽ የኢንፍሉዌንዛውን ቫይረስ ፣ ጨው እና ውሃን ብቻ የያዘ ነው። ክትባቱ የኢንፍሉዌንዛ በሽታን ሊያስከትል አይችልም። የኢንፍሉዌንዛው ክትባት ከኮሮና ቫይረስ ወይም ከሌሎች ቫይረሶች እና ባክቴሪያዎች አይከላከልም እነዚህ የኢንፍሉዌንዛ መሰል ምልክቶች ቢኖራቸውም።

**የጎንዮሽ ጉዳቶች**
የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች መርፌ በተወጉበት ቦታ ላይ መቅላት እና እብጠት እንዲሁም ትኩሳት ፣ መለስተኛ ህመም እና የጡንቻ ህመም ናቸው። ከኢንፍሉዌንዛ ክትባት በኋላ ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እና የአለርጂ ምላሾች የሚከሰትባቸው አጋጣሚዎች በጣም ጥቂት ናቸው።

**የኢንፍሉዌንዛ ክትባት የት መከተብ እችላለሁ?**
የአዋላጅ ሐኪምዎን ወይም የኮሚዩናውን ድርጣቢያ ይመልከቱ።

Norwegian Institute of Public Health

**ተጨማሪ መረጃ**

ስለ ኢንፍሉዌንዛ እና ክትባት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከታች ያለውን ድረ ገፅ ይመልከቱ።
www.fhi.no/en/id/influensa/seasonal-influenza/